Ee-JRIF

Ethiopian e-Journal
for Research and Innovation Foresight

**Vol. 9. no. 1, (2017) : pp (120 -133)**

# ለአድዋ ድል በቀል ለኢትዮጵያ ስለሚያስፈልገው ፍትሕ

ኪዳኔ ዓለማየሁ

## መግቢያ፤

እ.አ.አ. በየካቲት 1896 ባልተጠበቀና እጅግ አስገራሚ በሆነ መንገድ፤ ኢትዮጵያ፤ እስከዚያ ድረስ በየትኛውም ኣሕጉር ተደርጎ የማይታወቀውን፤ አንድ በመልማት ላይ ያለች ሐገር፤ የአንድ ጠንካራ የሆነ የአውሮፓ መንግሥትን፤ የኢጣልያን የጦር ወረራ በድል የተወጣች መሆኑ ለምን ጊዜም ቢሆን በውጭ ጠላት የማትበገር፤ የነጻነት ጮራ ሐገር መሆኗን አረጋግጦላታል። ስለዚህ ታሪካዊ አኩሪ ድል፤ ብዙ ተጽፏል፤ የአድዋ ክብረ-በዓል በሚዘከርበት ጊዜም፤ ዝርዝር ታሪኩና አንድምታው በሰፊው ይነገራል፤ ይጻፋል። የዚህ ጽሑፍ ትኩረት ግን፤ በመጀመሪያ፤ የአድዋው ጦርነት ዋናው መንስኤ ኢጣልያ ኢትዮጵያን የቅኝ ግዛቷ ለማድረግ የነበራት አጉል ምኞት ቢሆንም፣ የቀሰቀሰው አንደኛው ምክንያት የትርጉም ጠንቅ የነበረበት የውጫሌው ውል ስለ ነበር፤ ውሉ በአጼ ምኒልክና በኢጣልያኑ ተወካይ በአንቶኒሊ እንደ ተፈረመ፤ ወዲያውኑ በራስ መኮንን የተመራ አንድ የልዑካን ቡድን ወደ ኢጣልያ ተጉዞ ስለ ፈጸመው ጠቃሚ የዲፕሎማሲ ተግባር፤ ሁለተኛም አድዋ ላይ ለተከናነበችው እጅግ አሳፋሪ ሽንፈት፤ ኢጣልያ 40 ዓመት ሙሉ ጠብቃና ተዘጋጅታ፤ በቫቲካን ያልተቆጠበ ድጋፍ፤ በኢትዮጵያ ላይ ስለ ፈጸመችው አሰቃቂ የበቀል የጦር ወንጀል፤ ዳግመኛ ድል ብትነሳም፤ ለኢትዮጵያ ተገቢ የሆነ ፍትሕ ስለ አለመገኘቱና በመኪያሔድ ላይ ስላለው ትግል አጭር ዘገባ ይቀርባል። (1)[1]

## የውጫሌ ውል በተፈረመበት እለት፤

አጼ ምኒልክና የኢጣልያው ተወካይ፤ ፒየትሮ አንቶኒሊ፤ የውጫሌውን ውል የተፈራረሙት ሚያዚያ 25 ቀን 1881 ዓ/ም ነበር። (2)[2] ውሉን የተፈራረሙበት ዋናው ምክንያት አጼ ምኒልክ ከተቀናቃኞቻቸው ጋር ለመቋቋም ስለሚያስፈልጋቸው መሣሪያና የውጭ ድጋፍ የኢጣልያ ወዳጅነት የሚጠቅማቸው መሆኑን በመገመታቸው ነበር። ውሉ ሲፈረም፤ ራስ መኮንንም እዚያው ከአጼ ምኒልክ ጋር ነበሩ። ፔትራዲስ እንደ ዘገበው፡ (3[3])

> አጼ ምኒልክ፤ "…..ከሰዎቻችን ሁሉ የበለጠውን መርጠን መላክ አለብን። ምክንያቱም ጉዳዩ ጥበብ ሚያስፈልገውና በጣምም አስቸጋሪ ነው። አጎት የምንሆነውን ሰው፤ ወንድማችንና ወዳጃችን የሆነውን ደጃዝማች መኮንን ወልደ ሚካኤልን እንሾማለን።… ሌሎቹንም አብረውት የሚሔዱ መልእክተኞች እሱ ራሱ ይምረጥ።… እነዚህን ያጸድቁ ዘንድ እኛ ለኢጣልያ ንጉሥ ደብዳቤ እንጽፋለን"…ከዚያም በኋላ ሁለቱ (አጼ ምኒልክና ደጃዝማች መኮንን) በጣም ዝቅ ባለ ድምፅና በለዘበ አንደበት ንግግር ጀመሩ።

---

1 ለዚህ ጽሑፍ አንደኛው ምንጭ፤ "ቀኛዝማች አባ ናዳ - የኢትዮጵያ ጀግናና ዲፕሎማት"፤ 2001 ዓ/ም የጻፍኩት ነው። ስለ ፋሺሽት ኢጣልያና ከቫቲካን ጋር ስለ ነበራትም መተባበር በጻፍኳቸውም ድርሰቶች ተጠቅሜያለሁ።

2 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ "ዐጼ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት"፤ 1983፤ ገጽ 46

3 ፔትራዲስ፤ ኤስ. ጴጥሮስ፤ "የአድዋው ጀግና የልዑል ራስ መኮንን ታሪክ" 1961፤ ገጽ 86-87

ደጃዝማች መኮንን ውጪ ከወጡ በኋላ፤ “.......ወደ ኢጣልያ በማደርገው ጉዞ ከናንተ ሠላሳ ሰዎች ተከትለውኝ ይሔዳሉ። የነፍስ አባቴን ወልደ ሚካኤልን፤ አጎቴን አባዲን (አባ ናዳን)፤ አጎት የምሆነው ዘመዴን ቢራቱን፤ ቀኛዝማች ናደውንና ባላምበራስ ደሳለኝን ቶሎ መንገድ ይገቡ ዘንድ አስጠንቅቋቸው። በተቻለ መጠን ቶሎ እንነሳለን።”

PIC 1



በደጃች መኮንን (በኋላ ልዑል ራስ) መሪነት ኢጣልያ የተጓዙት የኢትዮጵያ ልዑካን። በመሀል ወምበሮች ላይ የተቀመጡት፤ ከግራ፤ ቀኛዝማች አባ ናዳ (የፈረስ ስም፤ የግል ስም፤ ቀኛዝማች ድልነሳሁ ጠንፉ)፤ አባ ወልደ ሚካኤል፤ ደጃዝማች (በጊዜው) መኮንን፤ እና ፊታውራሪ ቢራቱ። ፎቶግራፉ የተነሳው ናፖሊ ሲሆን መጀመሪያ የታተመውም L’Illustrazione Italiana በተሰኘው ጋዜጣ ላይ ነበር። (4)[4]

4 ቀኛዝማች አባ ናዳ በዘመኑ የኢጀርሳ ጎሮ ነዋሪና የአካባቢው ገዢ ነበሩ። ተፈሪ መኮንንም (በኋላ አጼ ኃይለ ሥላሴ) የተወለዱት እርሳቸው ቤት ሲሆን እድሚያቸው ሶስት ዓመት እስኪሆን ከምቦልቻ (ሐረርጌ) አባ ናዳ ወዳሠሩላቸው ቤት እስኪዛወሩ ድረስ ይኖሩ የነበሩት እዚያው ኢጀርሳ ጎሮ ነበር። አባ ናዳ የኔ ቅመ አያት ናቸው

**የልዑካኑ ጉዞ ዓላማና የኢጣልያኖች አቀባበል፤**

የጉዞው ዋና ዓላማ ሁለት ነበር። አንደኛው፤ የውጫሌው ውል በኢጣልያው ንጉሥ ኡምቤርቶ እንዲጸድቅ ለማድረግ እና ሁለተኛው ደግሞ ከኢጣልያ ብድር በማግኘት ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋትን የጦር መሣሪያ ለመግዛት ነበር። ልዑካኑ ኢጣልያ (ናፖሊ) የደረሱት እ.አ.አ. ሐምሌ 20 ቀን 1889 ሲሆን ወደ ሮም ከተማ በመጓዝ ከንጉሥ ኡምቤርቶ ጋር የተገናኙት እ.አ.አ. ነሐሴ 28 ቀን 1889 ነበር። ለልዑካኑ ስለ ተደረገው አቀባበል፤ በጊዜው ሥፍራው የነበሩት፤ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ፤ በተዋበ የጥንት አማርኛ፤ የዘገቡት ከዚህ እንደሚከተለው ነበር፤ "……….ደጃች መኮንን አርባ ሰው አስከትለው ወድ ኢጣልያ አገር ተሻገሩና የኢጣልያ ንጉሥ በክብር ሮማ ላይ ተቀበሏቸው። ያቀባበሉ ነገር በቃል ተነግሮ የሚጨርሱትና ጨርሶ በቃል የሚአስረዱት ነገር አይደለም። ግሩም እጹብ ድንቅ ነበረ። እስከ ረፋድ መንገድ ከሁለት እልፍ የበለጠ ጦር ተሰልፎ በጣልቂአ በጣልቂአው ባለ ሙዚካ ተሳከቶ ቁሞ መለኸቱ ነጋሪቱ እምቢልታው ሁሉ እየተነባበረ እየተመታ በመካከሉ ደጃች መኮንን እስከ ሰዋቸው በባለ ብር ጥሩር ሸልሜ ሰቀላ ሰቀላ በሚአካክል ፈረስ ተቀምጦ ተቀምጦ ደንገላሳ እየጋለበ ከንጉሡ አዳራሽ ደረሰ። ያ ሁሉ የንጉሥ ሸልሜ ከናት ማሕፀን እንደ ሰው የወጣ አይመስልም ነበረ።ብቻ በተለየ ሁለት ሁለቱን መዘዞ አንድነት እየጨፈለቁ ያበጁት ይመስል ነበረ። በግራ ክንዱ ጎሽ በቀኝ ክንዱ ዝሆን ለግቶ አላግቶ የሚጥል ይመስል ነበረ። ይሄው ሸልሜ የንጉሡ ዘበኛ ከንጉሡ ዙሪአ የማይለይ ምርጥ ሎሌ ነው። ይሄው ምርጥ ዘበኛ ደረቱ በክንድ ቁመቱ በገመድ የሚሰፈር የመሳሰለ ሸልሜ ነበረ። ከንጉሡ አዳራስ ሲደረስ ከደጃፉ ላይ ግራና ቀኝ የየጁን በርበሬ የመሰለ ጁህ ጁሁን ለብሶ ቅዱና ቅጡ ባበሻ ያልታወቀ ኩፍታ ኩፍታውን አድርጎ የብር የብር ጎመዱን ይዞ አጋፋሪ ቁሞ ነበረ። ደጃች መኮንን እስከ ሰዋቸው ተሰረገላ ወረዱና ከዚያ ሁሉ ሰልፍ መካከል ወዳዳራሹ ገቡ። ……………………..ከደረጃው መካከል ብቅ ሲባል የሰማይ ስባሪ የመሳሰለ መስተህት ዙሪአ ዙሪአውን እንቁጣጣሽ በመሰለ ወርቅ ተጣፍጦ ላይን ያሰክር እራስ ያዞር ነበረ።………………ደጃች መኮንን ሙሉ መሳርያቸውን አድርገው ሰዎቻቸውም አጊጠው አምረው ሄዱ ሄዱና የጉግሥ መጫወቻ ከሚአህል ወለል በደረሱ ጊዜ ……. እጅ ነሱ። ….. የኢጣልያ ንጉሥ በሸልሜው ታጥሮ በመኳንንቱ በሹማምቱ ተከቦ የመንግሥት ልብሱን ለብሶ ከመንበረ መንግሥቱ ላይ ተቀምጦ ነበረና እንዴት ዋላችሁ እንኳን ገባችሁ! አሰኘ። ከዚህ ወዲያ ………………..የኢትዮጵያንና የኢጣልያን ፍቅር ነገር ቃሉን በወረቀት አድርጎ ይዞ ነበርና አንብቦ ለደጃች መኮንን አሰማ። ንጉሡ ወዲያው አፈፍ ተነሣና ለደጃዝማች መኮንን እጁን ሰጠ ቀጥሎም ለፊታውራሪ ቢራቱ ሰጠ። ………….ደስ ብሎት ደስ አሰኝቶ ያበሻን መልክተኛ ተቀበለ።" (5)[5] የኢትዮጵያ መልእክተኞች ኢጣልያ የቆዩበት ጊዜ ከነሐሴ 1889 እስከ ሕዳር 1890 ለሶስት ወር ነበር። በዚሁ ጊዜ 11 ከተሞችን፤ ሮምን፤ ናፖሊን፣ ጀኖዋን፤ ቬኒስን፤ ቦሎኛን፤ ወዘተ. ጭምር ጎብኝተው ነበር።

---

5 አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ፤ "ዳግማዊ አጤ ምኒልክ"፤ 1901፤ ገጽ 66-69

## የጉብኝቱ ውጤት፤ የውጫሌው ውል ያስከተለው ጠንቅና የአድዋው የኢትዮጵያ ታላቅ ድል፤

በጊዜው፤ በደጃች መኮንን የተመራው የመልእክተኞች ቡድን ዓላማው ተሳክቶለት በተከናወነው ተጨማሪ ስምምነት 4 ሚሊዮን ሊሬ ብድር (6)[6] ከተገኘ በኋላ 28 ባለሰባ ሚሊ ሜትር ጠመንጃዎች፤ 38 000 ጠመንጃዎችና 2 500 000 ጥይቶች የሚገኙበት የጦር መሣሪያ ለመግዛት ችለው፤ ጉዟቸውን አጠናቅቀው፤ በኢየሩሳሌም በኩል ወደ ሐገር ተመለሱ። ስለዚህ፤ አንዱ አስገራሚ ጉዳይ፤ የአድዋው ድል የተገኘው፤ በኢትዮጵያዊያን ልውካን ዲፕሎማሲ በተገኘው የኢጣልያ የጦር መሣሪያ ጭምር በመጠቀም መሆኑ ነው። እንደሚታወቀው፤ በውጫሌው ውል ጠንቅ ያስከተለው አንቀጽ 17 ነበር። በዚህ አንቀጽ በኢጣልያንኛ የተካተተው እንደ አማርኛው ሳይሆን፤ ኢትዮጵያን የኢጣልያ ተገዢ ለማድረግ፤ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥቶች ጋር በምታከናውነው ግንኙነት በኢጣልያ መንግሥት አማካኝነት መፈጸም እንዳለባት የሚደነግግ ነበር። የኢጣልያንኛው አንቀጽ በኢትዮጵያ በኩል ሊታሰብ እንኳ የማይቻል ስለ ነበረ፤ በኢጣልያ በኩል ግን የቅኝ ግዛት ዓላማቸውን ለማሳካት የወረራ ተግባራቸውን በመቀጠላቸው የአድዋው ጦርነት ተከሰተ። የኢትዮጵያ መልእክተኞች ኢጣልያ በነበሩ ጊዜ፤ ኢጣልያንኛ የሚያውቁት፤ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ፤ ስለ አንቀጽ 17 ጠንቅ ለደጃች መኮንን አስገንዝበው ነበር። ስለዚሁ ጉዳይ፤ ጳውሎስ ኞኞ እንደ ጻፈው፡ (7)[7] "….በኢጣልያ አገር ሰዕል እንዲማሩ ተልከው የነበሩት ልጅ አፈወርቅ ገብረየሱስ (በኋላ ፕሮፌሰር የሆኑት) በጋዜጣ ያነበቡትን ለራስ መኮንን ነገሩዋቸው። ራስ መኮንንም አስጎብኚያቸው የነበረውን አንቶኒሊን ቢጠይቁት "……..ያ ደደብ ኢትዮጵያዊ ተማሪ ትርጉም ስላልገባው ነው" ብሎ ተሳደበ። ራስ መኮንንም ተቃውሞአቸውን ለኢጣሊያ መንግሥት ከነገሩ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ የውሉን መበላሸት ለአጤ ምኒሊክ አሳወቁ።" ለማንኛውም፤ በኢጣልያኖች በኩል፤ የውጫሌውን ውል እንደ ዘዴ ሊጠቀሙበት ሞከሩ እንጂ፤ ኢትዮጵያን የቅኝ ግዛታቸው ለማድረግ ቀድሞውኑ የወሰኑ በመሆኑ፤ የአድዋው ጦርነት ተከናውኖ ኢትዮጵያ ዓለምን ባስደነቀ ውጤት የተሟላ ድል ተጎናጸፈች። ያንንም ድል ያስገኙት የኢትዮጵያ አርበኞች ሁሉ በማይረሳ ውለታና አድናቆት ሁልጊዜም ይዘከራሉ። ኢትዮጵያም የነጻነት ጮራ ሆና፤ የባንዲራዋ ቀለሞች በብዙ የአፍሪካ ሐገሮች ተንጸባርቀው ይገኛሉ።

ስለ አድዋው ድል በጊዜው ከተደረሱት ግጥሞች መሀል፡ (8)[8]

"ምኒልክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ
ግብሩ እንቁላል ነበር ይኸን ጊዜ አበሻ።
በሠራው ወጨፎ ባመጣው እርሳስ
ተፈጠመ ጣልያን አበሻ እንዳይደርስ።
መድፉን መትረየሱን ባድዋ መሬት ዘርቶ
እንከርዳዱን ነቅሎ ስንዴውን ለይቶ
የዘራውን እህል አጭዶና ወቅቶ
ላንቶኒሊ አሳየው ፍሬውን አምርቶ።
እንዳቀና ብሎ ሰምኖ መሬት
ንግድ ሊያሰፋበት ሊዘራ አትክልት
እየመጣ ሊሰጥ ግብሩን ለመንግሥት
ለጓዙ ማረፊያ አገር ቢሰጡት
ተጠማኝ ሰንብቶ ሆኖ ባለርስት
ወሰን እየገፋ ጥቂት በጥቂት
እውነት እርስት ሆነው ተቀበረበት።
ባሕር ዘሎ መምጣት ለማንም አትበጅ
እንደ ተልባ ስፍር ትክዳለች እንጂ
አትረጋምና ያለተወላጅ።"

6 አበበ ሐይለመለኮት፣ The Victory of Adowa and what we ow to our heroes", 1998፣ ገጽ 74
7 ጳውሎስ ኞኞ፤ "አጤ ምኒልክ"፤ 1984፤ ገጽ 143
8 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ "አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት"፤ 1983፤ ገጽ 506


**የኢጣልያ የበቀል የጦር ወንጀል የቫቲካን መተባበር፤**

የአድዋው የኢትዮጵያ ድል ኢጣልያን እጅግ ከባድ የውርደት ማቅ አከናንቧት ነበር። ቢሆንም፤ የደረሰባትን ሽንፈት ሳትረሳ፤ የቅኝ ግዛት ዓላማዋን ሳትለቅ ከ 40 ዓመት ዝግጅት በኋላ፤ ኢጣልያ ኢትዮጵያን እ.አ.አ. በ 1935-41 ወረረች። በዓለም ሕግ በተከለከለ የመርዝ ጋዝ በብዙ አውሮፕላኖች በመነስነስና በልዩ ልዩ መሣሪያዎች በመጠቀም፤ በስቅላት፤ አንገት በመቁረጥ፤ በማቃጠል፤ ከአውሮፕላን በመወርወር፤ በማሰቃየት፤ ወዘተ. ፋሺሽት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ በፈጸመችው እጅግ የከፋ የጦር ወንጀል፤ የሚከተሉትን አሰቃቂ ጉዳቶች በሐገራችን ላይ እንዲከሰቱ አደረገች፤

(ሀ) አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ተገደሉ፤ ከነዚሁ ውስጥ፤ በግፈኛው ፋሺሽት ሮዶልፎ ግራዚያኔ ትእዛዝ በሶስት ቀኖች ብቻ፤ በአዲስ አበባ፤ 30 000 ኢትዮጵያውያን ተጨፈጨፉ። በወረራው ዘመን እነአቡነ ጴጥሮስ፤ አቡነ ሚካኤል፤ እጅግ ብዙ አርበኞች፤ ሴቶችና ሕጻናት ተሰዉ።

(ለ) 2 000 ቤተ ክርስቲያኖች፤ 525 000 ቤቶችና 14 ሚሊዮን እንስሳት ወደሙ።

(ሐ) እጅግ ብዙ የኢትዮጵያ ንብረቶች ተዘረፉ። ከነዚህ ውስጥ አሁንም ከ 500 ሰነዶች በላይ ቫቲካን ቤተመጻሕፍት ይገኛሉ። “ፀሀይ” የተሰኘች ኢትዮጵያ ተገጣጥማ የነበረች አንድ አውሮፕላንም በኢጣልያ አየር ኃይል ቤተ መዘክር እየታየች ነው።



በፋሺሽቶች ስቅላት የተሰዉ የኢትዮጵያ አርበኞች



ፋሺሽቶች የኢትዮጵያዊውን ራስ ቆርጠው በፈገግታ ሲያሳዩ

ከዚህ በታች በዝርዝር እንደሚቀርበው፤ ኢትዮጵያ ላይ በተፈጸመው የጦር ወንጀል፤ ቫቲካን ከነሙሶሊኒ ጋር እጅና ጓንት ሆና ሠርታ እንደ ነበር በብዙ ማስረጃ የተረጋገጠ ነው። የቫቲካን መሠረታዊ ዓላማም፤ ከነአጼ ሱስንዮስ ዘመን ጀምሮ የቀጠሉበትን ኢትዮጵያን የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ ለማድረግ ነበር። ባይሳካም ብዙ ጉዳት አድርሰዋል።

**ኢትዮጵያ ላይ ለተፈጸመው የጦር ወንጀል የፍትሕ ሁኔታ፤ ከሌሎች ሐገሮች ጋር ሲነጻጸር፤**

በአጠቃላይ፤ ፋሺሽት ኢጣልያ በቫቲካን ድጋፍ ለፈጸመችው ከባድ የጦር ወንጀል፤ ኢትዮጵያ ተገቢውን ፍትሕ አላገኘችም። በጊዜውም፤ ምንም እንኳ በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው የጦር ወንጀል በሌሎች ላይ ከተፈጸመው ጋር ሲወዳደር እጅግ የከፋና የላቀ ሆኖ ሳለ በፍትሕ ደረጃ ለኢትዮጵያ የተወሰነው ግን ኢምንት ነበር። ለዚህም ማስረጃ፤ እ.አ.አ. በ 1947 ኢጣልያ እንድትከፍል ተስማምታ የነበረው፤ ለዩጎዝላቪያ $125 ሚሊዮን፤ ለግሪክ ሐገር $105 ሚሊዮን፤ እና ለሶቪየት ሕብረት $100 ሚሊዮን ሲሆን ለኢትዮጵያ ግን የተወሰነው $25 ሚሊዮን ብቻ ነበር! የቆቃ ግድብ የተሠራውም በዚህ ገንዘብ ነበር። ከዚህ ሌላ ኢጣልያ የኢትዮጵያ ንብረት የሆነውን የአክሱም ሐውልት ከመመለሷ በላይ ተገቢውን ካሣ ሳትከፍል እና የተዘረፈውን ንብረትም ሳትመልስ ትገኛለች። እንዲያውም በንቀቷ ብዛት፤ ኢጣልያ ለግራዚያኒ፤ እንደ ጀግና፤ መታሰቢያ ሠርታለታለች! ቫቲካንም፤ በጊዜው የተቃውሞ ድምፅ ባለማሰማቷ ብቻ አይሑዶችን በመደጋገም ይቅርታ የጠየቀች ሆኖ ሳለ ኢትዮጵያን ግን እስካሁን ድረስ ይቅርታ ሳትጠይቅ ትገኛለች። እሥራኤል ብዙ ካሣ ተከፍላ፤ ይቅርታ ተጠይቃ፤ ያጠቋትም ተወንጅለዋል። ተመሳሳይ ጥቃት የደረሰባቸው ሌሎች ሐገሮች ምን እያከናወኑ ነው?

(ሀ) በቅርቡ፤ ኢጣልያ ለሊቢያ $5 ቢሊዮን ካሣ ለመክፈል መስማማቷ ተረጋግጧል።

(ለ) የጀርመን መንግሥት የናሚቢያን ሕዝብ ይቅርታ ጠይቃለች። በተጨማሪ፤ $3 ቢሊዮን ካሣ እንድትከፍል በናሚቢያ ተጠይቃለች፤

(ሐ) የኔዘርላንድስ መንግሥት ኢንዶኒዚያን ይቅርታ ጠይቃ ካሣ እየከፈለች ነው።

(መ) የእንግሊዝ መንግሥትም ኬንያውያንን ይቅርታ ጠይቃ ካሣ እየከፈለች ነው።

(ሠ) አርመኖች በኦቶማን ቱርኮች ለደረሰባቸው የአንድ ሚሊዮን ሕዝብ ጭፍጨፋ፤ ተገቢውን ፍትሕ ለማግኘት 100 ዓመት ሙሉ እየታገሉ ይገኛሉ። አርመኖች ለደረሰባቸው የቱርኮች የጦር ወንጀል 3 ትሪሊዮን የአሜሪካን ዶላር ካሣ ጠይቀዋል።

**በኢትዮጵያ ላይ ለተፈጸመው የጦር ወንጀል ቫቲካንና ፋሺሽት ኢጣልያ የነበራቸው ሕብረት፤**

በኢጣልያ የፋሺሽት እንቅስቃሴ ሲጀምር ከቫቲካን ጋር ተጻራሪዎች ነበሩ። በኋላ ግን እ.አ.አ. ከ 1922 ጀምሮ በጊዜው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን (የቫቲካን) መሪ የነበሩት፤ ፖፕ ፓየስ 11 ኛና የፋሺሽቶች መሪ የነበረው ሙሶሊኒ ወዳጅነት መሠረቱ። ዋናው ምክንያትም፤ ሁለቱም መሪዎች ለዲሞክራሲ፣ ለሶሺያሊዝም (ሕብረተሰባዊነት)ና ለኮምዩኒዝም ሥርዓቶች የነበራቸው ጥላቻ ነበር። በዚህም መሠረት፤ ቫቲካን የነበራትን የካቶሊክ ፓርቲ አስወግዳ የኢጣልያን ሕዝብ የፋሺሽቱን ፓርቲ እንዲደግፍ በይፋ ትንቀሳቀስ ጀመር። የቫቲካንንና የፋሺሽቶችን እጅና ጓንት ሆኖ መሥራት የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ከዚህ ቀጥሎ ይቀርባሉ፤

**1 ኛ/ እ.አ.አ. በ 1929 ቫቲካንና ፋሺሽቶቹ "ላተራን" (Lateran) የተሰኘውን ውል ተዋዋሉ። በዚህ ውል መሠረት ቫቲካን ለፋሺሽቱ ፓርቲ ሙሉ እውቅናና ድጋፍ ስትሰጥ፤ ፋሺሽቶቹ ደግሞ ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን (ለቫቲካን) ተመሳሳይ ድጋፍ ለማበርከት ዝግጁነታቸውን አረጋገጡ።**


ሙሶሊኒና የፖፕ ፓየስ 11 ኛ ተወካይ፤ አቡነ ጋሳፓሪኒ የ"ላተራን"ን ውል ሲፈራረሙ

**2 ኛ/ ቫቲካን ከላይ የተጠቀሰውን ውል በመፈረሟ፤ ከፋሺሽቶቹ መጠነ-ሰፊ ገንዘብ ያገኘች ሲሆን በተጨማሪም፤ ሕጋዊ ሉዓላዊነት ተፈቀደላት። አቭሮ ማንሓታን እንደ ጻፈው፤**

> (9)[9] "It was the alliance of these two men, Pius XI and Mussolini, that influenced so greatly the social and political pattern, not only of Italy, but also of the rest of Europe in the years between the two world wars."
> (ትርጉም፤ የነዚህ የሁለት ሰዎች፤ የፖፕ ፓየስ 11 ኛና የሙሶሊኒ ሕብረት ነበር በኢጣልያ ብቻ ሳይሆን በቀረው የአውሮፓ ክፍል ላይ በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መሀል በነበሩት ዓመቶች የማሕበራዊና የፖለቲካ ይዘት ከፍተኛ አጽንኦት ያሳደረው።)

በዚህ መሠረት፤ በሙሶሊኒ የተመራው የፋሺሽት ፓርቲ፤ በፖፕ ፓየስ 11 ኛ ያልተቆጠበ ድጋፍ፤ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ለፈጸመችው የወረራናየጦር ወንጀል ምን ያህል እንደ ጠቀማት መገንዘብ አያዳግትም።

**3 ኛ/ ሙሶሊኒ ለቫቲካን ያበረከተው የመጀመሪያው አገልግሎት 1.5 ቢሊዮን ሊሬ በማበርከት ነበር፤**

9 Avro Manhattan, "The Vatican in World Politics", 1947 (Chapter 9)

"The first service the ex-socialist rendered to the Holy See was a financial one. He saved the "Banco di Roma" to which the curia and many of its prelates had entrusted large amounts of money, from bankruptcy by stepping in with approximately 1.5 billion lire at the expense of the Italian state." (Karlheinz Deschner, "God and The Fascists", p31-32) (ትርጉም፤ የቀድሞው ሶሺያሊስት (ሙሶሊኒ) ለቫቲካን ያበረከተው የመጀመሪያው አገልግሎት የገንዘብ እርዳታ ነበር። በኢጣልያ መንግሥት ወጪ፤ 1.5 ቢሊዮን ሊሬ በማበርከት ቫቲካንና መንፈሳዊ መሪዎቿ ብዙ ገንዘብ ያስቀምጡ የነበረበትን "ባንኮ ዲሮማ"ን ከክስረት አዳነው።) Manhattan, 112) አቭሮ ማንሓታን በተጨማሪ እንደ ገለጸው፤

> "Thus the Church became the religious weapon of the Fascist State; while the Fascist State became the secular arm of the Church." (ትርጉም፤ ስለዚህ፤ ቤተ ክርስቲያኗ (የካቶሊክ) የፋሺሽቱ  መንግሥት ሃይማኖታዊ መሣሪያ ስትሆን፤ የፋሺሽቱ መንግሥት ደግሞ የቤተ ክርስቲያኗ ዓለማዊ ክንድ ሆነ።)

**4 ኛ/ ቫቲካን የፋሺሽቱን ጦር መባረኳ የማይጠረጠር ሐቅ ነው። ካቶሊኩ ካሕን ጦሩን ሲባርኩ የሚያሳየውን ፎቶ ከዚህ በታች መመልከት ነው፤**



የቫቲካኑ ካሕን የፋሺሽቱን ጦር ሲባርኩ

**5 ኛ/ ፋሺሽቶች በኢትዮጵያ ላይ ያከናወኑትን ወረራ፤ የመከላከል ጦርነት መሆኑን ፖፕ ፓየስ 11 ኛ ገልጸው ነበር።** የፋሺሽቱ ጦር አዲስ አበባ ሲደርስ፤ ከዚህ በታች የተጠቀሰውን የደስታ መግለጫቸውን እ.ኤ.አ. በግንቦት 12 ቀን 1936 በማወጅ፤ ፖፕ ፓየስ 11 ኛ በዚህ ረገድ ከዓለም መሪዎች ከመጀመሪያዎቹ አንዱ እንደ ነበሩ ተረጋግጧል፤

> "The triumphant joy of an entire, great and good people over a place which, it is hoped and intended, will be an effective contribution and prelude to the true place in Europe and the World." (15) (ትርጉም፤ ለአውሮፓና ለዓለም፤ መልካም ጅማሮና ሁነኛ ደረጃ ተገቢ አስተዋጽኦ እንዲሆን ለታቀደና ተስፋ ለተጣለበት ቦታ (ኢትዮጵያን ማለት ነው) የታላቅና ግሩም ሕዝብ (ኢጣልያኖችን ማለት ነው) ከፍ ያለ ደስታ።)

**6 ኛ/ የፖፕ ፓየስ 11 ኛን መግለጫ የበለጠ ያጠናከሩት ደግሞ የቱራኖ የካቶሊክ ጳጳስ ነበሩ። የሳቸው መግለጫ እንደሚከተለው ነበር፤**

> "The war against Ethiopia should be considered as a holy war, a crusade" (as Italian victory would) "open Ethiopia, a country of infidels and schismatics, to the expansion of the Catholic Faith." (ትርጉም፤ በከሐዲዎቹ ሐገር፤ በኢትዮጵያ፤ የካቶሊክን ሃይማኖት ለማስፋፋት ስለሚጠቅም፤ በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመው ጦርነት እንደ ቅዱስ ጦርነት፤ መንፈሳዊ ዘመቻ መቆጠር አለበት።)

**7 ኛ/ የሙሶሊኒና የፖፕ ፓየስ 11 ኛ ጠንካራ ሕብረት የተንጸባረቀበት ከባድ ክስተት በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመው የጦር ወንጀል ነበር።**

በቫቲካን በኩል፤ እነካርዲናል ኢልዲፎንሶ ሹስተር (ሚላን) (Cardinal Ildefonso Schuster of Milan) ኢትዮጵያን የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ ለማድረግና የኢጣልያን ግዛት ለማስፋፋት ወረራውን በይፋ ሲደግፉ በፋሺሽቶቹ በኩል ደግሞ ቁጥሩ እየጨመረ ለሔደው ለኢጣልያ ሕዝብ የቅኝ ግዛት ማስፈለጉን እንደ በቂ ምክንያት በማቅረብ ጦርነቱ እንዲከናወን ገፉበት። ፖፕ ፓየስ 11 ኛ የፋሺሽቱን ወረራ በሚቀጥለው ቋንቋ ደገፉት፤

"On August 27 (1935), when the Italian war preparations were running at full speed, the Pope announced interwoven in many calls for reason and peace-that a defensive war (!) for the purposes of the expansion (!) of a growing population could be just and right." (ትርጉም፤ እ.አ.አ. ነሐሴ 27 (1935) የኢጣልያ የጦርነት ዝግጅት እየተጧጧፈ ሳለ፤ ፖፑ (ፖፕ ፓየስ 11 ኛ)- ከተገቢነትና ከሰላም ጥያቄዎች ጋር እያወሳሰቡ፤ ታዳጊ ለሆነው የሕዝብ ብዛት ግዛትን ለማስፋፋት (!) የመከላከያ ጦርነት (!) ማከናወን ተገቢና ትክክል መሆኑን ገለጹ።" (ገጽ 43፤ ምንጭ፤ Manhattan, 121 pp. The speech is Printed in Reichspost, Vienna, August 30, 1935)

**8 ኛ/ ፖፕ ፓየስ 11 ኛ የፋሺሽቱን የኢትዮጵያ ወረራ የደገፉት ከላይ በተጠቀሰው መግለጫ ብቻ አልነበረም። ብዙ ሌሎች ተጨባጭ እርምጃዎች ወስደው ነበር። ከነዚህ ውስጥ፤**

(ሀ) ጳጳሶቹ የወርቅ መስቀሎቻቸውንና የአንገት ሰንሰሎቻቸውን እንዲያስረክቡ አዘዙ። በተጨማሪም፤ ጳጳሶቹና ካሕኖቹም የካቶሊክ ምእመናን ወርቆቻቸውንና ጌጦቻቸውን ለፋሺሽቱ መንግሥት ጦርነት እንዲያበረክቱ አደረጉ።

> "According to Professor Salvemini from Harvard University, at least seven Italian cardinals, twenty-nine archbishops, and sixty-one bishops supported the Fascist raid (on Ethiopia) immediately,….) (p. 46) (ትርጉም፤ የሐርቫርድ ዩኒቨርሲቲው ፕሮፌሰር ሳልቬሚኒ

(እንዳቀረቡት) ቢያንስ 7 (የካቶሊክ) ካርዲናሎች፣ 29 ሊቀ-ጳጳሶች እና 61 ጳጳሶች ወረራውን(በኢትዮጵያ ላይ) ወዲያውኑ ደገፉ።'' (ገጽ 46፤ ምንጭ Manhattan,)

(ለ) ጀርመን ሐገር የነበረው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ንብረት ለሙሶሊኒ እንዲዛወርና ለጦርነቱ የሚያስፈልገው እንዲገዛበት አደረጉ፤

(ሐ) ሌሎች ሐገሮች የሚገኙ ካቶሊኮች የኢጣልያን ወረራ እንዲደግፉ አደረጉ፤

(መ) የካቶሊክ ካሕናትና ሰባኪዎች ለኢጣልያ ጦር ድል እንዲጸልዩ ተደረገ፤

(ሠ) የፋሺሽት ወታደሮች፤ መድፍና የመርዝ ጋዝ በተጋዘበት መርከብ የቅድስት ማርያም ምስሎችም አብረው እንዲጓዙ ተደረገ፤

"…..Abyssinians, who had neither gas masks nor shelters, unsuspectingly fell victim to the dangers of Catholic culture. After the so-called Battle of Amba Aradam, an Italian captain counted more than sixteen thousand butchered "enemies" (Ethiopians). They lay there, dead or half-dead, where the skin-burning, lungtearing gas that was sprayed from the air had reached them, and they were all eliminated in the most hygienic possible way – that is, by flamethrowers. (p. 49) (ትርጉም፤ ጭንብልና መጠለያ የሌላቸው ያልጠረጠሩ ሐበሾች (ኢትዮጵያውያን) የካቶሊክ ባህል ሰለባ ሆኑ። አምባ አራዶም ከተሰኘው ጦርነት በኋላ አንድ የኢጣልያ ካፒቴን በቆጠረው መሠረት ከ 16 000 "ጠላቶች" (ኢትዮጵያውያን) በላይ ከአየር በተነሰነሰባቸው የመርዝ ጋዝ ቆዳቸው ተቃጥሎ፤ ሳምባቸው ተበጣጥሶ የሞቱ ወይም በመሞት ላይ የሚገኙ ነበሩ። ሁሉም በተወረወረባቸው የእሳት ቃጠሎ በቅልጥፍና ተወገዱ። (ገጽ 49፤ ምንጭ፤ Borgese, 400)

(ረ) ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣናቸውን ለኢጣልያን መንግሥት እንዲያስረክቡና በሚችራቸው ገንዘብ የተንደላቀቀ ኑሯቸውን እንዲቀጥሉ ብዙ ጉትጎታ አጋጥሟቸው ነበር። ስለ ፖፕ ፓየስ 11 ኛ ሙከራ፤ "Ethiopia Under Mussolini (Fascism and The Colonial Experience), 1985; በተሰኘው መጽሐፉ፤ አልቤርቶ ስባኪ (Alberto Sbacchi) ከእንግሊዝ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መዝገብ በመጥቀስ እንደሚከተለው ያተተው ነው፤

"……Father Cyril C. Martindale, the Jesuit scholar representing the Pope, confirmed that the secretary of state at the Vatican, Eugenio Cardinal Pacelli (later Pope Pius XII), offered Haile Selassie 1 million (Sterling Pounds) on behalf of Italy in return for his abdication." P 123

ትርጉም፤ የፖፑ ወኪል የነበሩት ጀስዊቱ ምሑር፤ አባ ሲሪል ሲ. ማርቲንዴል፤ ባረጋገጡት መሠረት የቫቲካን መንግሥት ዋና ጸሐፊ፤ ዩጂኒዮ ካርዲናል ፓቼሊ (በኋላ ፖፕ ፓየስ 12 ኛ) ኃይለ ሥላሴ ሥልጣናቸውን እንዲለቁ በኢጣልያን መንግሥት ስም አንድ ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ አቅርበውላቸው ነበር።

(ሰ) በኒው ዮርክ ታይምስ (New York Times) እ.አ.አ. የካቲት 13፣ 1937 በተዘገበው መሠረት፤ ፖፕ ፓየስ 11 ኛ በጊዜው የነበሩትን የኢጣልያ ንጉስ ኡምቤርቶን "የኢጣልያ ንጉሥና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት" በማለት የባረኳቸው መሆኑ ተገልጿል።

**ስለ ቫቲካን በኢትዮጵያ ጉዳይ ተጠያቂነት የቀረበ ሌላ አስተያየትና የተሰጡ መልሶች፤**

የቀድሞ አምባሳደር ዘውዴ ረታ፤ "የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት" በተሰኘ መጽሐፋቸው (ገጽ 295-315)፣ "የቫቲካን አቋም በኢትዮጵያ ጉዳይ" ምዕራፍ 16 ስር፤ በአጠቃላይ ፖፕ ፓየስ 11 ኛ በኢትዮጵያ ላይ ለተፈጸመው የፋሺሽት ግፍ ተጠያቂ አለመሆናቸውን ገልጸዋል። ይህ አባባል ከእውነት የራቀ መሆኑን የሚያረጋግጡ ብዙ ማስረጃዎች አቅርቤላቸዋለሁ። በተጨማሪም፤ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ምሑራን ስሕተታቸውን በመግለጽ አስተማማኝ ማስረጃዎችን አቅርበዋል፤

(ሀ) ቀሲስ/ዶር. ምክረሥላሴ ገ/አማኑኤል፤ "Church and Missions in Ethiopia During the Italian Occupation" (2014) በተሰኘ በእንግሊዝኛ በተደረሰ መጽሐፋቸው የፖፕ ፓየስ 11 ኛን ተጠያቂነት ፍንትው አድርገው አቅርበዋል።

(ለ) የዓይን ምስክርና የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑት፤ ዶር ሥዩም ገ/እግዚአብሔርም "An Eye Witness To the Collusion of the Vatican and Mussolini's Adventure in Ethiopia" በተሰኘ ጽሑፋቸው የፖፕ ፓየስ 11 ኛን ተጠያቂነትከማረጋገጣቸው በላይ፤ አምባሳደር ዘውዴ ስሕተታቸውን እንዲያርሙ ጠቁመዋል።

(ሐ) ሌላው የዓይን ምስክርና የኢትዮጵያ አርበኛ፤ ጀኔራል ለማ ገ/ማርያም፤ ለቀዳማዊ ፖፕ ፍራንሲስ በጻፉት ደብዳቤ፤ የቫቲካን ተጠያቂነት የማያጠራጥር በመሆኑ አይሑዶችን ይቅርታ እንደ ጠየቁት የኢትዮጵያን ሕዝብም እንዲጠይቁ አሳስበዋል።

(መ) የኦክላሆማ ስቴት ዩኒቪርሲቲ (Oklahoma State University) መምሕር የሆኑት ፕሮፌሰር ቴድ ቬስታል (Ted Vestal) ለኔ በጻፉት ሐተታ የቫቲካን ተጠያቂነት የማያጠራጥር መሆኑን አረጋግጠዋል።

(ሠ) ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን፤ ኮሎኔል ዮናስ ሊበን፤ ኤንጂኒየር ታደለ ብጡል፤ ወዘተ. በተመሳሳይ ዝርዝር ማስረጃ ስለ ቫቲካን ተጠያቂነት በማተት ጽፈዋል። ስለዚህ አምባሳደር ዘውዴ ረታ የጻፉት በጊዜው ባገኙት ውሱን ማስረጃ መሠረት በመሆኑ አሁን በማያወላዳ የቀረበውን ዝርዝር እውነት በመመልከት የእርምት መግለጫ አውጥተው አንባቢያቸውን ከማያስፈልግ ውዥንብር ቢያድኑ መልካም ነው።

**ለኢትዮጵያ ክብርና ፍትሕ ስለሚያስፈልገው ትግል፤ "ዓለም አቀፍ ሕብረት ለፍትሕ - የኢትዮጵያ ጉዳይ"**

Global Alliance for Justice – The Ethiopian Cause (www.globalallianceforethiopia.org)

ከላይ እንደ ተገለጸው፤ ኢትዮጵያ ለተፈጸመባት አሰቃቂ የጦር ወንጀልና ግፍ ተገቢ የሆነ ይቅርታ አልተጠየቀችም፤ አልተካሠችም። ለዚህ ከፍተኛ ዓላማና ተግባር የሚንቀሳቀስ "ዓለም አቀፍ ሕብረት ለፍትህ - የኢትዮጵያ ጉዳይ (Global Alliance for Justice – The Ethiopian Cause (www.globalallianceforethiopia.org) የተሰኘ ድርጅት በሰሜን አሜሪካ ተቋቁሞ በሰፊው እየተንቀሳቀሰ ነው። ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፤

(ሀ) ኢጣልያ ተገቢውን ካሣ ለኢትዮጵያ እንድትከፍል፤
(ለ) ቫቲካን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ፤
(ሐ) የኢጣልያና የቫቲካን መንግሥቶች በይዞታቸው የሚገኙትን የኢትዮጵያ ንብረቶች እንዲመልሱ፤
(መ) የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመውን የፋሺሽት የጦር ወንጀል እንዲመዘግብ፤
(ሠ) በኢጣልያ፤ አፊሌ በምትሰኝ ከተማ ለፋሺሽቱ ለግራዚያኒ በቅርቡ የተሠራው መታሰቢያና መናፈሻ እንዲወገድ።

ዓለም አቀፍ ሕብረት ለፍትሕ - የኢትዮጵያ ጉዳይ
**4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044, USA – (214)703 9022**
**www.globalallianceforethiopia.com** **info@globalallianceforethiopia.com**

**በሕብረቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮች፤**

1 ኛ/ ለኢትዮጵያ ስለሚያስፈልገው ፍትሕ ሰፊ ግንዛቤ እንዲገኝ፤ በድረ ገጹ በ www.globalallianceforethiopia.org በመጠቀም እንዲሁም ክልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙኃን ጋር በመተባበር ገለጻዎች ተከናውነዋል። ተጨማሪ ጥረት ያስፈልጋል።

2 ኛ/ በየዓመቱ፤ 30 ከተሞች ከሚገኙ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ጋር በመተባበር በየካቲት 12 ዝክር አማካኝነት ለሐገራችን ስለሚያስፈልገው ፍትሕ ትግሉ እየቀጠለ ነው።

3 ኛ/ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው፤ ለኢጣልያ መንግሥት ፕሬዚዳንት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፤ እንዲሁም ለተባበሩት መንግሥታት፤ አውሮፓ አንድነት ምክር ቤትና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅቶች የአቤቱታ ደብዳቤዎች ተጽፈው ክትትል እየተደረገ ነው።

4 ኛ/ ለቫቲካን፤ ለፖፕ ቤኔዲክት 16 ኛና አሁን በመምራት ላይ ለሚገኙት ለፖፕ ቀዳማዊ ፍራንሲስ እንዲሁም በቅርቡ በካርዲናልነት ለተሾሙት ለአቡነ ብርሃነየሱስ ደምረው ሱራፌል የአቤቱታ ደብዳቤዎች ከመጻፋቸው በተጨማሪ ከላይ በተጠቀሰው ድረ-ገጽ ላይ ቫቲካን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ የሚያመለክት አቤቱታ እየተፈረመ ነው። እስካሁን በ 30 ሐገሮች የሚኖሩ ከ 4 200 በላይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን፤ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ሌሎችም ዜጎች ፈርመውታል። የፊርማው ቁጥር 10 000 እስኪሆን ጥረቱ ይቀጥላል።

5 ኛ/ ማሕበሩ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢ.ኮ.ሶ.ክ. (ECOSOC: Economic and Social Council) የተባለ ታላቅ ድርጅት አባል ሆኗል።

6 ኛ/ ማሕበሩ ያቀናጀው ዓለም አቀፍ ጉባኤ በዋሺንግተን፤ ዲሲ ተከናውንቶ ለኢትዮጵያ ስለሚያስፈልገው ፍትሕ ጠንካራ ውሳኔ ተላልፋዋል።

7 ኛ/ የማሕበሩን እንቅስቃሴ የሚደግፉ ኢጣልያኖች

(ሀ) ስለ ፋሺሽቶቹ ግፍ የሚገልጽ አንድ ፊልም እያዘጋጁ ነው፤ እና

(ለ) በደብረ-ሊባኖስ የሚገኘው የሰማእታት መቃብር ተገቢው ጥብቃና ክብር እንዲያገኝ የመጸዳጃ ቤት ለመሥራትና አበባም እንዲተከልበት ለማድረግ የተግባር ሒደት ጀምረዋል።

8 ኛ/ ሮም የሚገኘው የድጋፍ ግብረ-ኃይል በፈጸመው ያላሰለሰ ጥረት (ሰላማዊ ሰልፍ፤ ጉባኤ፤ ወዘተ.) ለግራዚያኒ መታሰቢያ በመንግሥት በኩል ተመድቦ የነበረው በጀት ተቋርጧል፤ የአፊሌ ከተማ ከንቲባም እንዲከሰሱ ተወስኖ ስለ ኃውልቱ የተጀመረው ክስ በጥቅምት 2009 ዓ/ም ውሳኔ እንደሚያገኝ ይጠበቃል፤ መታሰቢያውም ለጎብኚዎች ተከልክሎ ተዘግቷል። ቢሆንም ጉዳዩ ገና በሙሉ ስላልተቋጨ፤ መታሰቢያው ጭራሹኑ እስኪወገድ ትግሉ ይቀጥላል።

**ትግሉን እንዴት ማገዝ ይቻላል ?**

ትግሉ ከባድ ስለ ሆነ፤ ለኢትዮጵያ ክብርና ተገቢው ፍትሕ እንዲገኝ የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ እንዲደግፉትና እንዲሳተፉበት ያስፈልጋል። ሊከናወኑ ከሚችሉት ተግባሮች ውስጥ፤

1 ኛ/ በድረ ገጹ ላይ የሚገኘውን አቤቱታ መፈረም፤

2 ኛ/ በየካቲት 12 ክብረ-በዓል መሳተፍ፤ ይኸውም በፀሎት፤ በስብሰባ እና/ወይም በሰላማዊ ሰልፍ ማከናወን፤

3 ኛ/ አውሮፓ የሚኖሩ ለኢትዮጵያ ፍትሕ የሚቆረቆሩ ሁሉ የአውሮፓ ምክር ቤት አባል የሆኑትን በማነጋገር ለሐገራችን የሚያስፈልገው ክብር እንዲገኝ ማድረግ፤

4 ኛ/ በሁሉም መንፈሳዊ ድርጅቶች የሚገኙ አማኞች ለሐገራችን ስለሚያስፈልገው ፍትሕ በቂ ግንዛቤ እንዲገኝ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ፤

5 ኛ/ ሌላም ጠቃሚ የሆነ እርምጃና ሐሳብ ማፍለቅና መተግበር።

**ማጠቃለያ፤**

የአድዋው ድል ኢትዮጵያውያንን ሁልጊዜም የሚያኮራ፤ ውድ ሐገራችን የነጻነት ነጸብራቅ መሆኗን የሚያረጋግጥ ነው። አኩሪ የሆነውን ድል ላስገኙልን የኢትዮጵያን መሪዎችና አርበኞች ሁሉም ትውልድ ሊያዘክርና ሊያወድሳቸው ይገባል። ሌላው፤ አብሮ መታየት ያለበት እውነት ግን፤ በአድዋው ድል የተዋረዱት ኢጣልያኖች ቂማቸውን ሳይረሱ 40 ዓመት ሙሉ ተዘጋጅተው በሐገራችን ላይ እጅግ አሰቃቂ ግፍና የጦር ወንጀል ፈጽመዋል። በኢትዮጵያ አርበኞች ተጋድሎና በእንግሊዞች ድጋፍ ዳግመኛ ሽንፈት ቢደርስባቸውም፤ የኢጣልያ መንግሥት፤ በቫቲካን ያልተቆጠበ ድጋፍ ስለ ፈጸመችው ወንጀል ኢትዮጵያ የሚገባትን ፍትሕ ሳታገኝ ቀርታለች። በፋሺሽቶች የተጨፈጨፉት የአንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ደም አሁንም እየጮኸ ስለሚገኝ በኢትዮጵያዊነታችን የምንኮራ ዜጎች ሁሉ ለሐገራችን ተገቢው ፍትሕ እንዲገኝ ትግላችንን አጠናክረን

መቀጠል ይገባናል።

**ለውድ ሐገራችን ለኢትዮጵያ የሚገበት ክብርና ፍትሕ እንዲገኝ ቸሩ አምላክ ይርዳን !**